# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነት በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ላይ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት፤

ሚያዚያ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

**ማውጫ**................................................................................................................................ I
**የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ (Executive Summery)** ........................................................................................ I
ክፍል አንድ................................................................................................................................ 1
መግቢያ................................................................................................................................ 1
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የሚገኙበቸው አካባቢዎች................................................................................. 3
በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ አምጪ ህዋሳት ስርጭት ............................................................... 3
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች............................................................................... 4
የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ራዕይና ተልዕኮ................................................................................... 4
የኢንስቲትዩቱ ራዕይ................................................................................................................ 4
የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ............................................................................................................. 4
የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ................................................................................................................ 5
የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ሥልጣንና ተግባር፡- ................................................................................. 5
የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ................................................................................ 7
ድርጅታዊ መዋቅር.................................................................................................................... 7
የኢንስቲትዩቱ የሰው ኃይል.......................................................................................................... 7
የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ ...................................................................................................... 7
የኦዲቱ አላማ................................................................................................................................ 8
ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)........................................................................ 8
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ........................................................................................ 9
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.................................................................................................................. 9
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ...................................................................................................................... 9
የኦዲቱ ወሰን ............................................................................................................................ 9
የኦዲቱ ዘዴ................................................................................................................................ 9
የቆላ ዝንብ እና ገንዲ በሽታ ምርምር የስራ ፍሰት ................................................................................ 10
ክፍል ሁለት ................................................................................................................................ 11
የኦዲት ግኝቶች ............................................................................................................................ 11
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ........................................................ 11
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መከላከልና እና የቁጥጥር ሽፋን ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፤............................................ 12
የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ፤.................................................................................. 20
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት የቴክኖሎጂዎች በቅንጅትን መጠቀምን በተመለከተ፤ ....... 21

በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ላይ የሚደረገው ምርምር ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 23
የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግኝዎች እና የኬሚካል ግብዓት ሥርጭትን በተመለከተ፤ ........ 24
ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ሥራ ላይ መዋላቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 27
ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና የኬሚካል ምርቶችን የሚያስወግድ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 29
ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራቱን በተመለከተ፣ ..... 30
ኢንስቲትዩቱ ለአርሶአደር፤ ለአርብቶአደርና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠቱን በተመለከተ፤ ........ 31
ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን የሰራ ስለመሆኑ፤ ........ 33
ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያግዝ መረጃ የሚያመነጭ እና የሚያደራጅ ስለመሆኑ፤ ... 34
በኢንስቲትዩቱ፤ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የሚታወቅና የአሠራር ስርዓት የተዘረጋለት ስለመሆኑ፤ ........ 36
ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፤ በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስተባብርና ስራዎቻቸውንም የሚያቀናጅ ስለመሆኑ፤ ........ 37
ክፍል ሦስት ........ 39
መደምደሚያ ........ 39
**ክፍል አራት** ........ 42
***የማሻሻያ ሃሳቦች*** ........ 42
አባሪ 1፡ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ድርጅታዊ መዋቀር ........ i
አባሪ 2፡ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር መዋቅር ........ ii
አባሪ ሦስት 3 የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ........ iii
***የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡ በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት*** ........ iii
***የኦዲቱ አካባቢ፡ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ፤*** ........ iii
አባሪ 4 ፡ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር የሥራ ፍሰት ........ vi
***2. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማስተባበሪያ ዴስክ*** ........ vi
***4. የአራቱ የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት ተግባር*** ........ vi
ሰንጠረዥ 1፡- መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ሥራ አፈፃፀም የሚያሳይ። ........ vii
ሰንጠረዥ ሁለት፡- የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከል ሥራ አፈፃፀምን የሚያሳይ። ........ vii

ሰንጠረዥ ሦስት፡- ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት  አፈፃፀምን የሚያሳይ።....................................................vii
ሰንጠረዥ አራት፡- መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ (የግሎሲና ፉስኪፐስ) ብዛት የሚያሳይ። ....................vii
ሰንጠረዥ አምሥት፡- መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ (የግሎሲና ፓሊዲፐስ) ብዛት የሚያሳይ። ............viii
ሰንጠረዥ ስድስት፡- በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ተነክሮ የተተከሉ ታርጌት ጨርቆች ቁጥርን የሚያሳይ። ..................viii
ሰንጠረዥ ሰባት፡-የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተቀቡ እንስሳትን የሚያሳይ።..........................................................viii
ሰንጠረዥ ስምንት፡-መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተረጨ (በካ.ኪ.ሜ) የሚያሳይ። ...........................viii

# የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ

## (Executive Summery)

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፤ በቃሊቲ ቆላ ዝንብ ምርምር ማዕከል፤ በአርባ ምንጭ የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና ቼክሊስት በመሙላት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ በአካል በመገኘት በምልከታ እና መረጃዎችን በመተንተን ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ እና በኢትዮጵያ የክዋኔ የኦዲት ስታንዳርድ እንዲሁም ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2014 እስከ 2017 ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡


በኦዲቱ ወቅት የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ ያለው አፈፃፀም ላይ የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡-


☞ በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ /፤ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ የስርጭት መጠንን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፍኖተ ካርታ /Road map/ የሚያሳይ መረጃ የሌለው መሆኑ፤

☞ ኢኒስቲትዩቱ በአስር አመት መሪ ዕቅድ በአዳዲስ መሬቶች ላይ መሰረታዊ መረጃ ሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ያቀደው እና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ የታቀደው መካከል ልዩነት ያለው መሆኑ፣





☞ ኢንስቲትዩቱ በአስር አመት መሪ ዕቅድ ላይ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል ያቀደው እና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ በ2016 የታቀደው መካከል ልዩነት ያለው መሆኑ፣





☞ በሶስቱ በጀት አመታት በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ከቆላ ዝንብና ከገንዲ የጸዳ መሬት ለመፍጠር የታቀደው ዕቅድና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ የታቀደው ያነሰ መሆኑ፤






☞ ከ2014-2016 በጀት አመታት በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ከቆላ ዝንብና ከገንዲ የጸዳ መሬት ለመፍጠር የታቀደው ዕቅድና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ የታቀደው ያነሰ መሆኑ፤




☞ የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ቴክኖሎጂዎችን (የመከኑ ዝንቦችን መልቀቅ ጨምሮ)፤ ኬሚካል የተቀቡ የታርጌት ጨርቆችን መትከል፤ ትራፖችን መትከል፤ መሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤ በአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ የማይጠቀም መሆኑ፤

☞ ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውል ግብዓቶች በተለይ የዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል አቅርቦት ኬሚካሉን መቀባት ከሚያስፈልጋቸው የእንስሳት ብዛትን (Animal Population) አንጻር በጣም አነስተኛ መሆኑ፤ ዴልታሜትሪን 20% ኬሚካል አቅርቦት ባለመኖሩ እና በወረዳዎች የታርጌት ተከላ አለመከናወኑ፤




☞ ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ሥራ ላይ ሳይውሉ የመጠቀሚያቸው ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች እና ሌሎች መወገድ ያለባቸው ንብረቶች መኖራቸው፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች

☞ ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን የመከላከልን የቁጥጥር ሥራውን የሚያግዝ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ፍኖተ ካርታ

ሊያዘጋጅና እርሱን ወደ ስትራቴጂክ ዕቅድ በመቀየር ሊተግብር ይገባል፡፡

- የኢንስቲትዩቱ በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ላይ ለማከናወን ያቀዳቸውን ነገር ግን ከመሪ ዕቅዱ አንጻር ዕቅድ አፈጻጸማቸው አነስተኛ የሆኑት፣ መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የሚጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ስፋት፣ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከል፣ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት ስፋት፣ መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች ብዛት፣ በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆች ተከላን፣ የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በእንስሳት ጀርባ መቀባትን፣ መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ርጭትን በተመለከተ፤ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር የተከናወነባቸው ወረዳዎች ብዛት፣ ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል ትራፖችን/ ወጥመዶችን በመትከል በተያዙት ላይ ጥናት ማካሄድን በቀሪው የመሪ ዕቅዱ አመታት እንዴት ማካካስና ዕቅዱን ለማሳካት የሚቻልበተን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ስልት በመቀየስና ወደ ትግበራ ሊገባ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ቴክኖሎጂዎችን (የመከኑ ዝንቦችን መልቀቅ ጨምሮ)፤ ኬሚካል የተቀቡ የታርጌት ጨርቆችን መትከል፤ ትራፖችን መትከል፤ መሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤ በአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት ቴክኖሎጂዎችን እንደየነባራዊው ሁኔታ መሰረት በማድረግ አቀናጅቶ ሊጠቀምና የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ እና በዕቅድ ያያዛቸውን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችና ኬሚካሎች ፍላጎት ጥናት ስትራቴጂካዊ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ግዥ ሊያከናውን እና የተገዙትም በተገቢው መንገድ ሊሠራጩና ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ብክነትን ጭምር መከላከል ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የአገልግሎት መስጫ ጊዜያቸው ኬሚካሎችን ከሚመለከታቸው እና የማስወገድ ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በኢንስቲትዩቱ ያሉ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና በተቀመጠው የህግ አግባብ መሰረት ሊያስወግድ ይገባል፡፡ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የቆላ ዝንብ ከሰሃራ በታች ባሉ 37 የአፍሪካ ሀገሮች ተሰራጭቶ የሚገኝ ሲሆን 23 ያህል ዝርያዎች ተለይተው የታወቁ መሆኑ በጥናት ተገልጿል፡፡ እነዚህ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች በሰው ላይ በአፍሪካ የእንቅልፍ በሽታ /sleeping sickness/ እንዲሁም በእንስሳት ላይ ገንዲ /naganeng/ የተባሉትን በሽታዎች በማስተላለፍ ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በማድረስ ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በኢትዮጵያም የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ በቆላ ዝንብ አማካኝነት በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ ምክንያት አርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ለም መሬቱን ለእንስሳትና ለእርሻ ልማት ለማዋል አዳጋች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ የቆላ ዝንብ ባለበት አካባቢ ሰፍረው የሚኖሩ ህዝቦችም በዚሁ በቆላ ዝንብ በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ ምክንያት የቀንድ ከብቶቻቸውና ሌሎች የቤት እንስሳቶቻቸው ምርታማ ሊሆኑ ባለመቻላቸው ያላቸው የእንስሳት ሀብት ሊኖራቸው ከሚችለው ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ከመሆኑም በላይ ከእንስሳት ሀብት የሚያገኙት ውጤትም እንደዚሁ ከሚጠበቀው በታች መሆኑ በጥናት ሰነዶች ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም የቀንድ ከብቶችን በመጠቀም በአካባቢው የእርሻ ልማት ለማካሄድ የሚደረገውን ጥረት በሽታውን የሚያስተላልፈው የቆላ ዝንብ መኖሩ የእርሻ ከብቶች ለገንዲ በሽታ መጋለጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ አድርሶበታል፡፡

2. የገንዲ በሽታን ለመቆጣጠር በአገራችን የተለያየ ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም፣ ጥረቶቹ በአብዛኛው ያተኮሩት ለበሽታው መፈወሻ የሚሆን መድሀኒት በመጠቀም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት መድሀኒቶቹ ለረዥም ጊዜ በጥቅም ላይ በመዋላቸውና አልፎ አልፎ በአግባቡ በጥቅም ላይ ባለመዋላቸው በአንዳንድ አካባቢዎች በሽታው መድሀኒቶቹን የመላመድና የመቋቋም ሁኔታ አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም በሽታውን በመድሀኒት ከመቆጣጠር በተጨማሪ የበሽታው አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘዴ ተግባራዊ ተደርጐ ቆይቷል፡፡ ይህም ዘዴ በአመዛኙ የዝንቧን ብዛት በፀረ ዝንብ ኬሚካል የመቀነስ አካሄድ ሲሆን፣ በተወሰኑ ቦታዎች ደግሞ የዝንብ ወጥመድ (Trap) በመጠቀም ጭምር ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በበሽታውም ሆነ በሽታውን በምታስተላልፈው ዝንብ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ላይ እንጂ በማጥፋት ላይ ያላተኮሩ ነበሩ፡፡

3. ከዚህም በመነሳት የገንዲን በሽታና አስተላላፊ የሆነውን የቆላ ዝንብ ለማስወገድ የሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ በተለየዩ የሰሜንና መካከለኛው አሜሪካ፣ በእስያ እንዲሁም በሰሜንና ምስራቅ አፍሪካ የፍራፍሬ ተባይና የእንስሳት በሽታ አስተላላፊ የሆኑ ዝንቦችን ለማጥፋት በሚደረግ ጥረት ላይ ተግባራዊ ሁነው ውጤታማነቱ ተረጋግጧል፡፡

4. በመሆኑም ይህን አዲስ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ ለማዋልና በሀገራችንም የቆላ ዝንብን ለማጥፋት በሚያስችል ነፍሳትን የማምከን ቴክኖሎጂ (The Sterile Insect Technique) አጠቃቀም አቅም በብሔራዊ ደረጃ ለመገንባትና በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ 25,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ ከገንዲና ቆላ ዝንብ ነፃ ለማድረግ የደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት በ1990 ዓ.ም በኢትዮጵያ መንግስትና በአለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ መካከል በተደረገ የጋራ ስምምነት ተቋቁሞ ነበር፡፡

5. በአገሪቷ ሀብትና ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ከሚታወቁ ዋና ዋና በሽታዎች መካከል አንዱ የሆነውን የገንዲ በሽታ በደቡብ የስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ በብሔራዊ ደረጃ እንዲመራ ብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 304/2006 የካቲት 20/2006 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡


6. ተቋሙ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር አጋርነት በመፍጠር የኢንስሳትን ጤና የሚያሻሽሉና የሚያሳድጉ ተግባራትን በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ተግባር ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ እንዲሁም ማዕከሉ በእንስሳት ጤና ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ከመፍታት አንፃር የተጣለበትን ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት በተለይም የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ላይ ያሉትን የጤና ችግሮች በምርምርና በጥናት በመለየትና መረጃዎችን ወደ ሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ በማድረግ ለዘርፉ ውጤታማነት ጥረት ሲያደርግ ቆይተዋል፡፡

7. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም መሠረት የብሔራዊ የእንስሳት ምርመራና ጥናት ማዕከል እና ብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት ተዋህደው የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ተብሎ እንዲቋቋሙ ተወሰነ፡፡

በዚህም መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንስቲትዩቱን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባራትን በመወሰን በደንብ ቁጥር 503/2014 ተቋቋመ ፡፡

## የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የሚገኙባቸው አካባቢዎች

8. በኢትዮጵያ በአጠቃላይ በቆላ ዝንብ አማካይነት በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ የተጠቁ አካባቢዎች ሀገራዊ መረጃ እንደሚያሳየው ከ200,000 እስከ 240,000 ካ.ኪ.ሜ ከአጠቃላይ የመሬት ስፋት 18% /በመቶ/ እንደሚገመት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡




## በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ አምጪ ህዋሳት ስርጭት

9. በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች በዋነኛነት አምስት ሲሆኑ በቆላ ዝንብ ተጠቂ በሆኑት ስምንት ክልሎች ውስጥ ቢንስ ሦስት አይነት የዝንቡ ዝርያ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

| የክልሉ ስም | በክልል የሚገኝ የዝርያው አይነት |
|---|---|
| በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል (አሁን ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች) | G.M. Submorsitans, G. pallidipes, G.f.fuscipes and G.longipennis |
| በኦሮሚያ ክልል | G.M.Submorsitans, G.pallidipes, G.techinoides and G.f.fuscipes |
| በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል | G.M. Submorsitans, G.pallidipes, G.f.fuscipes and G.techinoides፣ |
| በጋምቤላ ክልል | G.pallidipes, G.techinoides and G.f.fuscipes |
| በአማራ ክልል | G.M.Submorsitans and G.techinoides |

10. በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የገንዲ በሽታ ህዋሳት Trypanosome vivax; T.brucei; T. congolense ግመሎችን የሚያጠቃ T.evansi እና በጋማ ከብቶች በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ T. equiperdum በመባል የሚታወቁ ህዋሳት ይገኙባቸዋል፡፡

## የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች

11. በኢንስቲትዩቱ ስር ያሉ ማዕከላት የቆላ ዝንቦችን ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ስራ ላይ በአካባቢ ላይ የጎላ ጉዳት የማያደርሱ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም፡-

- በእንስሳት ጀርባ ላይ ኬሚካል መቀባት፤
- ኬሚካል የተቀቡ የታርጌት ጨርቆችን መትከል፤
- ትራፖችን መትከል፤
- መሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤
- በአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት በማካሄድ
- በገንዲ በሽታ ለታመሙ እንስሳት ህክምና መስጠት እንዲሁም
- የቆላ ዝንቦችን በብዛትና በጥራት በማራባት እና የቆላ ዝንብ ቅነሳ የተካሄደባቸው አካባቢዎች በጨረር ኃይል የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን በመልቀቅ የመጨረሻውን ዝንብ የማጥፋት ስራ በመጠቀም ነው፡፡

## የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ራዕይና ተልዕኮ

### የኢንስቲትዩቱ ራዕይ

12. በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ በእንስሳት ጤና ምርምር፤ ምርመራ፤ የበሽታ ቁጥጥር እና ስልጠና የልህቀት ማዕከል መሆን፤

### የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ

13. አገራችን በውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተጠቃሚ እንድትሆን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ በመጠቀም፤ እንዲሁም አግባብነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የእንስሳት ጤና ምርምር፤ ምርመራ፤ የበሽታ ቁጥጥር፤ የስልጠና እና የማማከር ሥራዎችን ውጤታማ፤ ተደራሽና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ በማከናወን የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ነው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ዓላማ

14. የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የተቋቋመባቸው አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ☞ የእንስሳት በሽታ፤ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበረሰባዊና አካባቢያዊ ጉዳት ከማስከተሉ በፊት መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል የምርምርና ምርመራ ስራዎችን በማከናወን አገሪቷ ከእንስሳት ሀብቷ በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተጠቃሚ እንዲትሆን ማድረግ፤
- ☞ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ በተጠቁ የአገሪቱ አካባቢዎች የመከላከል፤ የመቆጣጠር እና የማጥፋት ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ በማካሄድ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤
- ☞ በእንስሳት ጤና ላይ የሥልጠናና የማማከር ስራዎችን በማከናወን በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን አቅም እንዲጎለብት ማድረግ ነው፡፡

## የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ሥልጣንና ተግባር፡-

15. በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 503/2014 ዓ.ም. የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ተሰጥቶታል ፡፡

- ☞ ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበረሰባዊና አካባቢያዊ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ የእንስሳት ጤና ችግሮች ላይ የሚካሄድ ምርምርን ያስተባብራል፤ የምርምርና ስርፀት ሥራዎችን ያካሄዳል፤ ይገመግማል፤ ያስተዋውቃል፤ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
- ☞ በምርምርና ምርመራ ግኝት መሠረት የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር ስልት በመለየት ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፤
- ☞ ከሌላ ሀገር በእንስሳት ጤና ምርምር የተገኘ ቴክኖሎጂን ያላምዳል፤
- ☞ በባህላዊና ዘመናዊ የእንስሳት መድኃኒት ላይ ምርምር ያካሂዳል፤
- ☞ በሀገር ውስጥ የእንስሳት ጤና የሪፈራል ምርመራ ላቦራቶሪ በመሆን የመጨረሻ ማረጋገጫ ይሰጣል፤
- ☞ በሀገራችን ውስጥ ለሚገኙና ድንበር ዘለል ለሆኑ የእንስሳት በሽታዎች እና ነፍሳት፤ አዳዲስና ተደጋግመው የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን የመከላከልና የቁጥጥር ሥራዎችን ለመደገፍ የስጋት ትንተና፤ አሰሳና ቅኝት፤ እና የበሽታ ስርጭትና የጉዳት መጠን ግምገማ ያካሂዳል፤

- የእንስሳት በሽታ ክስተት መንስዔን ይለያል፤ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤ ያስጠነቅቃል፤ እንዲሁም መረጃዎችን ያሰራጫል፤
- ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ የእንስሳት በሽታዎች ላይ የምርምርና ምርመራ፤ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ያከናውናል፤
- ለእንስሳት በሽታ ምርመራ የሚያግዝ የላቦራቶሪ ግብዓት ያበለጽጋል፤ ቴክኖሎጂ ያመነጫል፤ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ እንዲሁም በግብዓት ማበልጸግና ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን ያበረታታል፤
- እንስሳት ወደ ሌላ ሀገር በሚላኩበት ጊዜ ወይም ወደ ሀገራችን ሲገቡ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የጤንነት ማረጋገጫ ምርመራ ያካሂዳል፤ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የምርመራ ውጤት ይሰጣል፤
- የክልል እንስሳት ጤና ላቦራቶሬዎችን አቅም ለማጎልበት በትብብር ይሰራል፤
- የእንስሳት ጤናን በተመለከተ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች፤ ተቋማትና ለግል ባለሀብቶች የምክር አገልግሎትና፤ የአጭር ጊዜና የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፤ ለረጅም ጊዜ ሥልጠና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፤
- የእንስሳት ጤና መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያከማቻል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ያድርጋል፤ መረጃውንም በህትመት፤ በኢንስቲትዩቱ በይነ-መረብ፤ በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች ዘዴዎች አማካይነት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤
- የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ የቁጥጥር ዘዴዎችንና ስልቶችን ይለያል፤ የመከላከል፤ የቁጥጥርና ማጥፋት ሥራዎችን ያከናውናል፤ ውጤቱንም ተከታትሎ ይገመግማል፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የጨረር ቴክኖሎጂን ለእንስሳት ጤና ምርምር፤ ለበሽታ ምርመራና ቁጥጥር ዓላማ ይጠቅማል፤
- ለእንስሳት በሽታ ምርምርና ምርመራ የሚውሉ ናሙናዎች፤ የቆላ ዝንቦችና ሌሎች ባዮሎጂካል ውጤቶችን የሀገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል፤ ይጠቀማል፤ ወደ ውጭ ሀገሪም ይልካል፤

- ☞ አግባብነት ባለው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ እና ከዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ምርምርና ምርመራ ተቋማት እና አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር ይሰራል፤
- ☞ የምርምርና ምርመራ ሥራዎችን ብቃትና ጥራት በይበልጥ ለማጎልበት ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኙ አሠራሮችን እና ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤
- ☞ ለምርምርና ምርመራ የሚያገለግሉ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ጥገና ክፍል በማደራጀት ወደ ሥራ ማስገባት የሚሉ ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

16. የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፤ በዋና ዳይሬክተር፣ ሁለት ም/ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን አንድ የጽ/ቤት ኃላፊ፣ አነድ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ስድስት መሪ አስፈጻሚ፣ ዘጠኝ ሥራ አስፈጻሚ እና በአምስት ማዕከሎች ተዋቅሯል፡፡ **(ዝርዝሩ በአባሪ 1 እና አባሪ 2 ተያይዟል)**

### የኢንስቲትዩቱ የሰው ኃይል

17. ለኢንስቲትዩቱ በጠቅላላው በመዋቅር 910 የሰው ሀይል የተፈቀደ ሲሆን፤ 434 የሥራ መደብ ያልተሸፈነ ሲሆን፤ አምስቱንም ማዕከል ጨምሮ በመጋቢት 2016 ዓ.ም 476 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 169 (35.5%) ሴቶችና 307 (64.4%) ወንዶች ናቸው፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ፤ ፒኤችዲ 3 (0.63) በማስተርስ ደረጃ ያሉ 69 (14.49%)፤ የመጀመሪያ ድግሪ 140 (29.4%)፣ ዲፕሎማ 38 (7.98)፤ ደረጃ አራት 50 (10.5%)፤ የቀለም ትምህርት ያላቸው ሰራተኞች 176 (36.97%) እንዲሁም ከአጠቃላይ ሰራተኞች የኮንትራት ሰራተኛ ቁጥር 9 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 2 (22.22 %) ሴቶችና 7 (77.77%) ወንዶች ነበሩ፡፡

## የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ

18. የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ሥራውን የሚያከናውነው በመንግስት ከሚመደብለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት ሲሆን፤ ከ2014-2016 ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና ያወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**መደበኛ በጀት**

| በጀት ዓመት | የተፈቀደ በጀት | ጥቅም ላይ የዋለ | በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 2014 | 128,350,545.83 | 101,032,928.35 | 78.72 | |
| 2015 | 176,336,492 | 143,931,831 | 81.6 | |
| 2016. | 192,604,437 | 193,996,120.68 | 100.7 | |

**ካፒታል/ፕሮጀክት/ በጀት**

| በጀት አመት | ካፒታል | ጥቅም ላይ የዋለ | በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 2014 | 10,409,471.42 | 3,585,373.41 | 34.44 | |
| 2015 | 20,720,760 | 3,489,866.45 | 16.84 | |
| 2016. | 21,385,902 | 24,572,869.24 | 114.9 | |

**የኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ጤና ፕሮግራም /ፕሮጀክት/ በጀት የፋይናንስ ምንጭ ሰንጠረዥ**

| በጀት ዓመት | ፕሮግራም/ፕሮጀክት/ በጀት ዓይነት | የፀደቀና የተስተካከለ በጀት (ብር) | ሥራ ላይ የዋለ በጀት (ብር) | የፋይናንሻል አፈፃፀም በመቶኛ | የፊዚካል አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 | ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቅነሳ ሥራ | 42,976,495 | 34,734,075.93 | 81 | 55 |
| | ለምርምርና ጥናት ሥራ | 45,037,545.83 | 38,136,682.65 | 84 | 96.6 |
| | ድምር | 88,014,040.83 | 72,870,758.58 | | |
| 2015 | በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቅነሳ ሥራ | 67,148,716.83 | 65,381,504.58 | 97.37 | 80 |
| | ለምርምርና ጥናት ሥራ | 20,598,099.36 | 10,037,800.24 | 48.73 | 82 |
| | ድምር | 87,746,816.19 | 75,419,304.82 | | |
| 2016 | ቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቅነሳ ሥራ | 67,638,313. | 66,990,499.25 | 99 | 85 |
| | ለምርምርና ጥናት ሥራ | 21,252,182 | 20,674,561.93 | 97.2 | 94 |
| | ድምር | 88,890,495 | 87,665,061.10 | | |
| 2017 | ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቅነሳ ሥራ | 63,289,040 | 3,025,560 | 64.75 | 50 |
| | ለምርምርና ጥናት ሥራ | 27,053,240 | 465,288.15 | 39.01 | 75 |
| | ድምር | 90,342,280 | 3,490,788.15 | | |

## የኦዲቱ አላማ

19. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፤ ቀልጣፋና፤ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ያለመ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ እንዲሁም ተጠያቂነተን ለማስፈን ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

20. በግብርና ሚኒስቴር "የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነት" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

21. ከላይ የተጠቀሰውን የኦዲት አካባቢ ለመገምገም ሦስት ዋና ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/፤ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፦

1. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የመከላከል፤ የመቆጣጠር እና የማጥፋት እንዲሁም የምርምር ሥራ አፈፃፀም ውጤታመነትን መገምገም፤
2. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች፤ ሥርጭት እና የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ስርዓት ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም፤
3. ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ በተጠቁ የአገሪቱ አካባቢዎች የመከላከል፤ የመቆጣጠር እና የማጥፋት ስራዎች ዙሪያ ሕብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኝ ስለመደረጉና የባለድርሻ አካላት ተሣታፊ ስለመሆናቸው መገምገም፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡ (**የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ-3 ተያይዘዋል**)

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

22. ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ዋና ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 23 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ (የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 3 ተያይዘዋል፡፡)

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

23. ኦዲቱ የተከናወነው በአለማቀፍ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች መሰረት (International Performance Audit Standards) እና በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2014 እስከ 2017 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያለውን የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነት" የሥራ ክንውኖች ነዉ፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

24. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት በእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የተከናወነ ሲሆን በስሩ በሚገኙ በቃሊቲ ቆላ ዝንብ ምርምር ማዕከል፤ በአርባ ምንጭ የእንስሳት ጤና

ምርምር ማዕከል፣በጋሞ ዞን፣ በወላይታ ዞን፣ በምህራብ አባያ ወረዳ፣ በአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ በኦፋ ወረዳ እና በአበላ አባያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና ቼክሊስት በመሙላት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በመከለስ፣ በአካል በመገኘት በምልከታ እና መረጃዎችን በመተንተን ነው፡፡

## የቆላ ዝንብ እና ገንዲ በሽታ ምርምር የስራ ፍሰት

25. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ አሰሳና ቅኝት መረጃን በማደራጀት፣ የተቀናጀ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ከስሩ የተዋቀሩት ዴስኮችና ጣቢያዎችን በማስተባበር እንዲሁም ከሌሎች የክልል፣ የዞንና የወረዳዎች የእንስሳት ዘርፍ ተቋማት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትን በመፍጠር የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት የሚሰሩ ናቸው፡፡ **(የስራ ፍሰቱን የሚያሳይ ዝርዝር በአባሪ 5 ተያይዟል፡፡**

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤

26. ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፍኖተ ካርታ ሊያዘጋጅና ለትግበራው ሊያጠናና ስትራቴጂ ሊነድፍ ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችን፣ የአኗኗር ባሕሪያቸውንና የመኖሪያ ሥፍራቸውን መሰረት ያደረገ የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድርስ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዝርያዎች በተመለከተ የቁጥጥሩና የቅኝት ሥራውን ለማከናወን፡-

- ☞ በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፣ፍኖተ ካርታ /Road map/፣ የስርጭት መጠንን የሚያሳይ መረጃ የሌለው መሆኑ፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት የስትራቴጂክ ዕቅድ ያለዘጋጀ እና ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች እና ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭት መጠን የአሥር ዓመት መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት በዓለም ዓቀፍ ጆርናል ላይ እ.ኤ.አ 2022 የታተመው የክልሎችን የስርጭት መጠንን የሚያሳይ እና የአምስት ዓመት መረጃ በቀጣይ እ.ኤ.አ 2025 ለማሳተም ዕቅድ የያዙ መሆኑን፣ እና የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ፍኖተ ካርታ /Road map/ እ.ኤ.አ ከ2025 ጀምሮ በሚተገበረው ስትራቴጂ ሰነድ ጋር የተዘጋጀ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

29. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት ከ2005-2017 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ከ2012 እስከ 2025) የተዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ ረቅቂ እስከ 2017 ግማሽ በጀት ዓመት ለአሥራ ሦስት ዓመት አለመፅደቁና ተግባራዊ አለማድረጉ እንዲሁም የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ

መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ፍኖተ ካርታ /Road map/ ያልተካተተበት በመሆኑ፤ እ.ኤ.አ. ከ2025 ጀምሮ ይተገበራል የሚለውን መልስ ጊዜው ለመጠናቀቅ ወራት ብቻ የቀር በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

30. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት የስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ አለማድረጉ እና በብሔራዊ ደረጃ የተዘጋጀ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ የስርጭት መጠንን የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ /Road map/፤ አለመኖሩ ለችግሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

31. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት የተዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊ አለመደረጉ እና የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ ፍኖተ ካርታ /Road map/፤ አለመኖሩ የዝንቦቹን የስርጭት መጠን እንዳይታወቅና የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታን ለመከላከልና ለማጥፋት አዳጋች አድርጎታል፡፡

**የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መከላከልና እና የቁጥጥር ሽፋን ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ፤**


32. ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ተጠቂ የሆኑ ቆላማና ከፊል ቆላማ አካባቢዎችን ተደራሽ በማድረግ የመከላከል እና የቁጥጥሩን ሽፋን ሊያሳድግ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማከናወን የተዘጋጀውን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ወደ አመታዊ ዕቅድ በመመንዘር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ❖ በምዕራብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች ከ75,000 ካ.ኪ.ሜ በላይ የሚገመት ከስድስት ዓመታት በላይ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ስራዎች በመቋረጡ ምክንያት በቆላ ዝንቦች ዳግም የተወረረ መሆኑ፤ ኢንስትቲዩቱ አዲስ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ስራ የሚሠራባቸው መሬቶችን ያላስፋፋ መሆኑ፤ ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ተጠቂ የሆኑ ቆላማና ከፊል ቆላማ አካባቢዎችን ተደራሽ ያላደረገ እና የቁጥጥር ሽፋኑን ያላሳደገ መሆኑ፤ ለአብነት፡-

***መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶችን በተመለከተ፤***

- ☞ ኢኒስቲትዩቱ በአስር አመት መሪ ዕቅድ በአዳዲስ መሬቶች ላይ መሰረታዊ መረጃ ሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ያቀደው እና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ የታቀደው በማነስ ልዩነት ያለው መሆኑ፣




☞ በ2014 በጀት ዓመት መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች 10,976 ካ.ኪ.ሜ ለማከናወን አቅዶ 11,058 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን ከመቶ በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅድ (2013-2022) በ2014 በጀት ዓመት 17,746 ካ.ኪ.ሜ አከናውናለው ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 62.3 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

☞ በ2015 በጀት ዓመት መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች 11,000 ካ.ኪ.ሜ ለማከናወን አቅዶ 4,700 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን 42.7 ከመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2015 በጀት ዓመት 15,777 ካ.ኪ.ሜ መሠረታዊ መረጃ እሰበስባለሁ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 29.7 በመቶ ብቻ መሆኑ፤


☞ በ2016 በጀት ዓመት መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች 9,346 ካ.ኪ.ሜ ለማከናወን አቅዶ 3,650 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን 39.1 ከመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት 15,871 ካ.ኪ.ሜ መሠረታዊ መረጃ እሰበስባለው ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 22.9 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

| ዓ.ም | አመታዊ ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ክንውን | ከአመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | የአሥር ዓመት ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ከአሥር ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 | 10,976 | 11,058 | +100 | 17,746 | 62.3 (11,058) |
| 2015 | 11,000 | 4,700 | 42.7 | 15,777 | 29.7 (4,700) |
| 2016 | 9,346 | 3,650 | 39.1 | 15,871 | 22.9 (3,650) |
| ድምር | 31,322 | 19,408 | 61.96 | 49,394 | 39.29 (19,408) |

ሰንጠረዥ 1፡- መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ሥራ አፈፃፀም የሚያሳይ፡፡ (ከኢንስቲትዩቱ የ10 ዓመት ዕቅድና አመታዊ ዕቅድ የተወሰደ እና የተተነተነ)

**የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከልን በተመለከተ፤**

☞ ኢኒስቲትዩቱ በአስር አመት መሪ ዕቅድ ላይ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል ያቀደው እና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ በ2016 የታቀደው መካከል ልዩነት ያለው መሆኑ፣ **በ2016 በጀት ዓመት** የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል 55,000 ካ.ኪ.ሜ መሬት ለመሸፈን አቅዶ 75,717 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን ከመቶ ፐርሰንት በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት 106,920 ካ.ኪ.ሜ አከናውናለው ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 70.8 በመቶ ብቻ መሆኑ፤




**ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬትን በተመለከተ፤**


☞ በ2014 በጀት ዓመት ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት 72,202 ካ.ኪ.ሜ ለማከናወን አቅዶ 50,338.95 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን 70 በመቶ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2014 በጀት ዓመት 87,800 ካ.ኪ.ሜ አከናውናለው ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 57.3 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

☞ በ2015 በጀት ዓመት ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት 80,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ለማከናወን አቅዶ 51,277 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን 64.1 በመቶ የፈፀመ

መሆኑ፤እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2015 በጀት ዓመት 110,520 ካ.ኪ.ሜ አከናውናለሁ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 46.39 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

- ☞ በ2016 በጀት ዓመት ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት 35,000 ካ.ኪ.ሜ ላይ ለማከናወን አቅዶ 35517 ካ.ኪ.ሜ በማከናወን ከ100 በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት 114,605 ካ.ኪ.ሜ መሬት አፀዳለው ብለው ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 30.5 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

- ☞ በሶስቱ በጀት አመታት በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ከቆላ ዝንብና ከገንዲ በሽታ የጸዳ መሬት ለመፍጠር የታቀደው ዕቅድና ወደ አመታዊ ዕቅድ ተመንዝሮ የታቀደው ያነሰ መሆኑ፤





**መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች በተመለከተ፤**


- ☞ በ2014 በጀት ዓመት መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ብዛት የግሎሲና ፉስኪፐስ 202,000 አቅዶ 86,300 በማከናወን 43 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2014 በጀት ዓመት የግሎሲና ፉስኪፐስ በቁጥር 1,595,400 አመክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 5.4 በመቶ ብቻ መሆኑ፤ እንዲሁም የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 250,000 አቅዶ 328,490 በማከናወን ከመቶ በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅድ በ2014

በጀት ዓመት የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 1,700,760 አመክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 19.3 በመቶ ብቻ መሆኑ፤

☞ በ2015 በጀት ዓመት መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ብዛት የግሎሲና ፉስኪፐስ 186,472 አቅዶ 147,123 በማክናወን 78.9 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅድ በ2015 በጀት ዓመት የግሎሲና ፉስኪፐስ በቁጥር 1,595,724 አመክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 9.2 በመቶ ብቻ መሆኑ፤ እንዲሁም የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 370,000 አቅዶ 533,193 በማክናወን ከመቶ በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ ይሁን እንጂ በአሥር አመት እቅዱ በ2015 በጀት ዓመት የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 1,702,106 መክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብለው ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 31.3 በመቶ ብቻ መሆኑ፤


☞ በ2016 በጀት ዓመት መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ብዛት የግሎሲና ፉስኪፐስ 211,932 አቅዶ 288,070 በመልቀቅ ከመቶ በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት የግሎሲና ፉስኪፐስ በቁጥር 1,559,745 አመክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 18.46 በመቶ ብቻ መሆኑ፤ እንዲሁም የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 632,045 ለመልቀቅ አቅዶ 305,759 በመልቀቅ 48.37 በመቶ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም በአሥር አመት እቅድ በ2016 በጀት ዓመት የግሎሲና ፓሊዲፐስ በቁጥር 1,702,126 መክኖ መስክ ላይ ይለቀቃሉ ብለው ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር 17.96 በመቶ ብቻ መሆኑ፤




**በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆች ተከላን በተመለከተ፣**

- በ2014 በጀት ዓመት በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆችን በቁጥር 36,723 ለመትከል አቅዶ 3,281 ታርጌቶችን በመትከል 8.9 በመቶ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣
- በ2015 በጀት ዓመት በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆችን በቁጥር 32,000 ለመትከል አቅዶ 369 ታርጌቶችን በመትከል 1.2 በመቶ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣
- በ2016 በጀት ዓመት በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆችን በቁጥር 4000 ለመትከል አቅዶ ምንም የታርጌት ተከላ ያላከናወነ መሆኑ፣




**የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በእንስሳት ጀርባ መቀባትን በተመለከተ፣**

- በ2014 በጀት ዓመት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በ3,133,600 እንስሳት ጀርባ ላይ ለመቀባት አቀዶ 1,389,598 እንስሳት በመቀባት 44.4 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፣
- በ2015 በጀት ዓመት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በ3,620,000 እንስሳት ጀርባ ላይ ለመቀባት አቀዶ 1,590,605 እንስሳት በመቀባት 43.9 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፣
- በ2016 በጀት ዓመት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በ3,880,000 እንስሳት ጀርባ ላይ ለመቀባት አቀዶ 1,661,528 እንስሳት በመቀባት 43 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፣





**መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ርጭትን በተመለከተ፤**

☞ በ2014 በጀት ዓመት መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል 18,900 ካ.ኪ.ሜ ለመርጨት አቅዶ 180 ካ.ኪ.ሜ በመርጨት 1.0 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤

☞ በ2015 በጀት ዓመት መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል 23,800 ካ.ኪ.ሜ ለመርጨት አቅዶ ምንም ርጭት ያላከናወነ መሆኑ፤

☞ በ2016 በጀት ዓመት መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል 1,500 ካ.ኪ.ሜ ለመርጨት አቅዶ ምንም ርጭት ያላከናወነ መሆኑ፤




**የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር የተከናወነባቸው ወረዳዎችን በተመለከተ፤**

☞ በ2014 በጀት ዓመት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር በ184 ወረዳዎች ላይ ለማከናወን አቅዶ በ130 ወረዳዎች ላይ በማከናወን 71 በመቶ ያከናወነ መሆኑ፤

☞ በ2015 በጀት ዓመት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር በ233 ወረዳዎች ላይ ለማከናወን አቅዶ 205 ወረዳዎች ላይ በማከናወን 80 በመቶ ያከናወነ መሆኑ፤

☞ በ2016 በጀት ዓመት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ተግባር በ164 ወረዳዎች ለማከናወን አቅዶ በ165 ወረዳዎች በማከናወን ከመቶ በላይ የፈፀመ መሆኑ፤ይሁን እንጂ በ2015 በጀት ዓመት ከደረሰበት አፈፃፀም አንፃር 80.48 በመቶ መሆኑ፤

| ዓ.ም | ዕቅድ በቁጥር | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 184 | 130 | 71 |
| 2015 | 233 | 205 | 80 |
| 2016 | 164 | 165 | +100 |
| ድምር | 581 | 500 | 86.05 |

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር የተካሄደባቸው ወረዳዎችን የሚያሳይ፡፡

**ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል ትራፖችን/ ወጥመዶችን በመትከል በተያዙት ላይ ጥናት ማካሄድን**

☞ በ2014 ዓ.ም ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል 10,300 ትራፖችን/ ወጥመዶችን ለመትከል አቅዶ 2,682 በማከናወን 26 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ የገንዲ በሽታ ሥርጭት ጥናት ለማድረግ 39,250 የደም ናሙና ለመውሰድ አቅዶ 16,973 በበሽታ ተጠቂ ሆነው የተገኙትን እንስሳት የቀይ የደም ህዋስ መጠናቸው (PCV) ከ20 በታች ወርዶ ለተገኙት እንስሳት የህክምና አገልግሎት በመስጠት 43.24 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም የቆላ ዝንቦችን የውስጥ አካል በመክፈት ጥናት (Dissection) በቁጥር 5,610 ለማከናወን አቅዶ 1,823 ዝንቦች የውስጥ አካል በመክፈት 33 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤

☞ **በ2015** ዓ.ም ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል10,500 ትራፖችን/ወጥመዶችን ለመትከል አቅዶ 5,956 በማከናወን 56.7 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤ እንዲሁም የቆላ ዝንቦችን የውስጥ አካል በመክፈት ጥናት (Dissection) በቁጥር 5,120 ለማከናወን አቅዶ 2,460 ዝንቦች የውስጥ አካል በመክፈት 48 በመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፤ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩት በሀገራችን ስምንት ክልሎች ውስጥ አምስት ማዕከላትንና አራት ጣቢያዎችን

በመዘርጋት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ስራዎች በስፋት እየሰራ እንደምገኝ እና አጠቃላይ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ተደራሽ ለማድረግ በፀጥታ ችግር ምክንያት የተቆራረጠ ቢሆንም የማዕከላትን አቅም በማጠናከር ሁሉንም አካባቢዎች ተደራሽ እንዲሆን ኢንስቲትዩቱ በቀጣይ በትኩረት የሚሰራ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

35. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡ በኢንስቲትዩቱ የአስር አመት መሪ ዕቅድ መሰረት አመታዊ ዕቅዶች ለምን እንዳልታቀዱ ምላሽ ባለመስጠታቸው፣ አዲስ የቆላ ዝንብ ማጥፋት ስራ የሚሠራባቸው መሬቶችን ያላስፋፉ በመሆኑ፤ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ስራዎችን በስፋት እየሰራው ነው፤ የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

36. ኢንስቲትዩቱ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠርና ማጥፋት ሥራ የ10 አመት መሪ እቅድን መሰረት አድርጎ ባለማቀዱና ያቀዳቸውንም የአንዳንዶቹ አፈጻጸም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የቁጥጥሩ ሽፋን አነስተኛ መሆኑ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

37. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠርና ማጥፋት ሥራ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅተው በመጠቀም ዝንቡን የመቀነስ ሥራ በተከታታይነት ባለመሥራቱ በቆላ ዝንብና በገንዲ በሽታ የተጠቁ ቦታዎች ከሰራባቸው በኃላ ዳግም እንዲጠቁ እና የቁጥጥሩ ሽፋን እንዳያድግና የህብረተሰቡ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዳያድግ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

38. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የስርጭት ካርታ ሊያዘጋጅና በየጊዜው ሊያሻሽል ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን ቆላማና ከፊል ቆላማ የስራ አካባቢን /Operational area/ መሠረት በማድረግ የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የስርጭት ካርታ አዘጋጅቶ ጆርናል ላይ ከማሳተም ባለፈ ለዋናኛ ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፤ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ኢንስቲትዩቱ የ10 ዓመት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭት የሚያሳይ በጆርናል ላይ የታተመ መሆኑንና የተሻሻለ የሥርጭት ካርታ በጆርናል ላይ ለማሳተም በሂደት ላይ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

41. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭት የሚያሳይ ካርታ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታን የመካለከልና የመቆጣጠር ሥራ ላይ ለተሰማሩት እንዲሁም ለሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲደርስና ሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በመሆኑ እንዲሁም በጆርናል ላይ መታተሙ ብቻ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራው ላይ ውጤት የማያመጣ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግቷል፡፡

42. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን ቆላማና ከፊል ቆላማ የስራ አካባቢን /Operational area/ መሠረት በማድረግ የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በጆርናል ላይ የታተመው የስርጭት ካርታ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ አለመደረጉ ለችግሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

43. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን ቆላማና ከፍል ቆላማ የስራ አካባቢን /Operational area/ መሠረት በማድረግ የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የስርጭት ካርታ ተዘጋጅቶ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ለሚሰሩ አካላት እንዲደርስ አለመደረጉ የመከላከል ሥራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማድረጉም በላይ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭት እንዳይታወቅ አድርጎታል፡፡

**የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት የቴክኖሎጂዎች በቅንጅትን መጠቀምን በተመለከተ፣**

44. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ያሉትን ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ ሊጠቀም እንዲሁም በየደረጃው ያሉ አካላትም ይህንኑ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

45. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንቦችን በማዕከላቱ አማካኝነት የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ሲያከናውን የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ቴክኖሎጂዎችን (የመከኑ ዝንቦችን መልቀቅ ጨምሮ)፣ ኬሚካል የተቀቡ የታርጌት ጨርቆችን መትከል፣ ትራፖችን መትከል፣ መሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት

ማካሄድ፣ በአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ የማይጠቀም መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-

✓ ኢንስቲትዩቱ ከቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ቴክኖሎጂ ውስጥ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል በሰፊው እየተሰራ መሆኑ፣ መሬት ለመሬት ኬሚካል ርጭት፣ ኬሚካል የተነከረ ታርጌት የመትከል ሥራ በኬሚካል እጥረት ምክንያት የተቋራረጠ መሆኑ፣ የመካን ነፍሳት ቴክኖሎጂ በደቡብ ኢትዮጵያ ደሜ ተፋሰስ እየተሰራ መሆኑ፣ እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ (STEP) ፕሮጀክት አጠቃላይ 25,000 ካ.ኪ.ሜ. ላይ የቆላ ዝንብን ለማጥፋት የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለሙከራ 1000 ካ.ኪ.ሜ. በደሜ ተፋሰስ የተጀመረና የዚህን ተሞክሮ ወደ ሌሎች አጎራባች ወረዳዎች ለማስፋፋት የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦች የሚለቀቁበት ድሮን ወደ ስራ ለማስገባት ረጅም ጊዜ የወሰደ መሆኑ፣ ነግር ግን በሌሎች የቁጥጥር ስራዎች የተገኙት ውጤቶች የግብርና ሥራዎች እና ለእንስሳት እርባታ ሥራዎች ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

47. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ

☞ በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ ማዕከላት የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ቴክኖሎጂ ውስጥ በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ኬሚካል ብቻ ላይ እየሰሩ በመሆኑ፣ መሬት ለመሬት ኬሚካል ርጭት፣ ኬሚካል የተነከረ ታርጌት መትከል በኬሚካል እጥረት ምክንያት ሥራው የተቋረጠ በመሆኑ፣ ሁለትና ከዛ በላይ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅተው እየተጠቀሙ ስላልሆነ፣

☞ የመካን ነፍሳት ቴክኖሎጂ በደቡብ ኢትዮጵያ ደሜ ተፋሰስ ሥራን በተመለከተ፣ የገንዲ በሽታን ለመጨረሻ ግዜ ለማጥፋት የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን በመጠቀም በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ፕሮጀክት ተቀርጾ በ1990 ዓ.ም ሥራ የጀመረ ቢሆንም ፕሮጀክቱ በታቀደው መሰረት ውጤታማነት ስለመገምገሙና በግምገማው ውጤት መሰረት ለቀጣይ ሥራዎች እንዲውሉ

ስለመደረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከሃያ ስድስት አመታት በኃላም ለሙከራ 1,000 ካ.ኪ.ሜ. በደሜ ተፋሰስ ስራ ተጀምሯል የሚለውን መልስ አሳማኝ ባለመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

48. በኢንስቲትዩቱ ሥር የሚገኙ ማዕከላት የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ በቀላል ተቀናጅተው መከላከልና ቁጥጥር መስራት የሚቻላቸውን ቴክኖሎጂዎች አለመቀናጀቱና፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ (STEP) ፕሮጀክት አፈጻጸም መልካም ተሞክሮው አለመወሰዱና የተቀናጀ ቴክኖሎጂን የማይጠቀሙና ከ25,000 ካ.ኪ.ሜ የቆላ ዝንቦችን ከ90-95% በመቀነስና በቀጣይ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ስራ በመስራት አካባቢው ለእንስሳት እርባታና ለእርሻ ልማት አመቺ አለማድረጉ እና ሥራው ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ውጤት ያላስገኘ መሆኑን እንዲሁም ከሃ ስድስት አመታት በ1,000 ካ.ኪ.ሜ. በደሜ ተፋሰስ አሁንም ሙከራ ላይ መሆኑ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

49. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ አለመጠቀም የቆላ ዝንቦችና የገንዲ በሽታ ስርጭት እንዲቀንስ ያላደረገ እና በጨረር ኃይል የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን በመልቀቅ የመጨረሻውን ዝንብ የማጥፋት ስራ እንዳይሳካ በማድረግ ለእንስሳት እርባታና ለእርሻ ልማት አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል ፡፡

## በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ላይ የሚደረገው ምርምር ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

50. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን ቀርፆ ጥናትና ምርምር ሊያካሂድና ውጤቱንም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

☞ ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ጤና ምርምር ስትራቴጂ እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድረስ ያላዘጋጀ መሆኑ፤

☞ በኢንስቲትዩቱ የገንዲ ፓራሳይት ማከሚያ መድኃኒቶች መላመድ ምክንያት እንስሳት ከገንዲ በሽታ እየዳኑ ባለመሆኑ አማራጭ መፍትሔ ጥናትና ምርምር ያላደረገ መሆኑ፣

☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድርስ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናትና ምርምር ያላደረገ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፤ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡-ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ስራዎች የኢኮኖሚ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያቶች በለጋሽ ድርጅቶች እንዲጠና የገንዘብ ድጋፍ ተጠይቆ በቂ ምላሽ ባለማግኘቱ በመንግስት በኩል የምርምር በጀት እንድፈቀድ ፕሮፖዛል አዘጋጅቶ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር አቅርቦ ምላሽ እየተጠበቀ እንደምገኝ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

53. በኢንስቲትዩቱም ሆነ ዕቅድ በመያዝና በጀት በመጠየቅ በራስ ኃይልና ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የተከናወኑ ሥራዎች ያስገኙት ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ጥናት አለማድረጉ እንደምክያት ተወስደዋል፡፡

54. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን አለመከናወናቸው እየተከናወኑ ያሉ የመከላከልና የቁጥጥር ሥራዎች ያስገኙት ፋይዳ እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

### የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች እና የኬሚካል ግብዓት ሥርጭትን በተመለከተ፤


55. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ፍላጎት ጥናት ሊሰበስብ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

☞ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት ለአርባ ምንጭ ማዕከል፣ለሶዶ ማስተባበሪያ ጣቢያ፣ለጋሞ ዞን፣ ለወላይታ ዞን፣ ለምዕራብ አባያ ወረዳ፣ ለአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ ለጎፋ ወረዳ እና ለአበላ አባያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ፣ኢንስቲትዩቱ ወይም ለማዕከሎቹ የሚያቀርባቸው ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ የኬሚካል አቅርቦት በወቅቱ የማይቀርብና በቂ አለመሆኑን ለቀረበላቸው መጠይቅ የማዕከልና የማስተባባሪያ እንዲሁም የግብርና መምሪያና ጽ/ቤት ኃላፊዎች መግለጻቸው፣

☞ ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ፣ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውል ግብዓቶች ፍላጎት ጥናት ከማዕከላት በመሰብሰብ ከ2014 እስከ 2017 በጀት ዓመት የሚገዛቸው በእንስሳት ጀርባ ላይ የሚቀባ ዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል የእንስሳት ብዛትን (Animal Population) መሰረት ያላደረገና በቂ አለመሆኑ፣ ለአብነት፡-

☞ በ2016 በጀት ዓመት የማዕከላት የኬሚካል ግዥ ፍላጎትን በተመለከተ፡- አርባምንጭ ዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል 30,000 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20%፣1,300 ሊትር፣ በደሌ ማዕከል ዴልታሜትሪን 1%፣ 20,000 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20%፣ 2,000 ሊትር ፣አሶሳ ማዕከል ዴልታሜትሪን 1%፣ 6,000 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20%፣ 300 ሊትር ፣ ፍኖተሰላም ማዕከል፡- ዴልታሜትሪን 1%፣ 4,000 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20%፣ 100 ሊትር አራቱ ማዕከላት በጠቅላላ ዴልታሜትሪን 1%፣ 60,000 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20%፣ 3700 ሊትር እንዲገዛላቸው የጠየቁ ቢሆንም በ2016 በጀት የተገዛው ለአራቱ ማዕከላት በጠቅላላ ዴልታሜትሪን 1%፣ 20,000 ሊትር ከፍላጎት አንፃር 33.33 በመቶ ብቻ መሆኑ እና ዴልታሜትሪን 20%፣ 2,250 ሊትር ከፍላጎት አንፃር 60.8 በመቶ ብቻ መሆኑ፣




- ☛ ባለፉት አራት ዓመታት (ከ2013-2016) በሶስት ማዕከላት (አርባ ምንጭ፤ በደሌ እና አሶሳ) ዴልታሜትሪን 20% ኬሚካል አቅርቦት አለመኖሩ፤

የቆላ ዝንብ ከፍተኛ ስርጭት ባለባቸው ወረዳዎች የታርጌት ተከላ ያልተከናወነ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች፤ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ዴልታሜትሪን 20% ቀደም ስል ለሦስት ዓመታት በዶላር እጥረት ምክንያት ግዥ ያልተፈፀመ ሲሆን በ2016 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱ ኬሚካል በመግዛት ማዕከላት ሥራ ውስጥ የገቡ ቢሆንም የተገዛው ኬሚካል ከፍላጎት አንፃር በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፤ በ2017 ዓ.ም 27,000 ሊትር ለመግዛት ጫራታ ወጥቶ በሂደት ላይ ያለ ቢሆንም አሁንም ለመግዛት የታሰበው ከፍላጎት አንፃር በጣም ዝቅተኛ መሆኑና በ2016 በጀት ዓመት ከተገዛበት ዋጋ ከእጥፍ በላይ በመጨመሩ ለመግዛት የታሰበውን መጠን 35,000 ሊትር እንዳይገዙና የቆላ ዝንብ መከላከል ሥራውን አስቸጋሪ እንዳደረገባቸው ገልፀዋል፡፡

58. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውል ግብዓቶች ዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል የእንስሳት ብዛትን (Animal Population) መሰረት አለማድረጉና እንዲሁም ዴልታሜትሪን 20% ኬሚካል እጥረት በመኖሩ በወረዳዎች የታርጌት ተከላ አለመከናወኑ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

59. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፣ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውል ግብዓቶች ዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል የእንስሳት ብዛትን (Animal Population) መሰረት አስቀድሞ ግዥውን ሁል ጊዜ የሚያስፈልጉ በመሆኑ የግብአቶቹ ዕጥረት የተቋረጠ እንዳይሆን ስትራቴጂ ቀርጾ እንቅስቃሴ አለማድረጉና በወረዳዎች የታርጌት ተከላ አለመከናወኑ የቆላ ዝንብ ስርጭት ለመቀነስ ሆነ የገንዲ በሽታን መከላከልን አዳጋች አድርጎታል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ሥራ ላይ መዋላቸውን የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ፣

60. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ለተገዙበት አላማ መዋላቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

61. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ❖ ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ለተገዙበት አላማ ያልዋሉ መሆኑ፣ ለአብነት፡-
  - ☞ በኢንስቲትዩቱ መጋዝን ዴልታሜትሪን 1% 40 ሊትር የአንዱ ዋጋ = 40 x 530.22= 21,208.8 እ.ኤ.አ Apri,2021 እና ዴልታሜትሪን 20% 160 ሊትር የአንዱ ዋጋ = 160 x 1315.40= 210,464 እ.ኤ.አ Feb,2020 የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ መሆኑ በጠቅላላ 200 (ሁለት መቶ) ሊትር = ብር 231,672.8 የሚያወጡ ኬሚካሎች ሥራ ላይ በወቅቱ ሳይውሉ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ (Expaired) መሆኑ፣
  - ☞ በአርባ ምንጭ እንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል ዴልታሜትሪን 1% 604 ሊትር የአንዱ ዋጋ = 604 x 530.22= 320,252.88 እ.ኤ.አ April,2021 እና ዴልታሜትሪን 20% 2646 ሊትር የአንዱ ዋጋ = 2646 x 1315.40 = 3,480,548.40 እ.ኤ.አ Feb,2020 የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ (Expaired) መሆኑ በጠቅላላ 3250 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ አምሳ) ሊትር = ብር 3,800,801.27 የሚያወጡ ኬሚካሎች ለተገዙት አላማ ሳይውሉ በአርባ ምንጭ ማዕከል እና በሶዶ ማስተባበሪያ ጣቢያ መጋዝን ከ19/05/2012 ጀምሮ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን በመስክ ጉብኝት ወቅት የተገኘ መሆኑ

ኬሚካሎቹ የአገልግሎት ጊዜ ሶስት ወር ሲቀራቸው የደረሳቸው መሆኑን መግለጻቸው፤

☞ እንዲሁም በአሶሳ እንስሳት ጤና ማዕከል ዴልታሜትሪን 20%= 268 ሊትር የአንዱ ዋጋ = 268 x 1315.40 በጠቅላላ ብር 352,527.20 የሚያወጣ ኬሚካል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው /expired/ የሆኑ ኬሚካሎች አገልግሎት ላይ ሳይውል ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፤ ከመስክ ምልከታ እና ከቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡

62. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ለቆላ ዝንብ ቁጥጥር ሥራ የሚውሉ ግብዓቶን በተመለከተ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች የሚወገዱበት ሥርዓት የለሌ በመሆኑ፤ እንደ ሀገር የኬሚካል አወጋገድ መመሪያ እየተጠየቀ መሆኑን የኢንስቲትዩቱ የስራ ኃላፊዎች የገለፁ ሲሆን የአርባ ምንጭ ማዕከል እና የሶዶ ማስተባበሪያ ጣቢያ ኬሚካሎቹ የአገልግሎት ጊዜ ሶስት ወር ሲቀራቸው ለምን እንደተላካለቸው ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

63. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ አርባ ምንጭ ማዕከል እና ሶዶ ማስተባበሪያ ጣቢያ ኬሚካሎቹ የአገልግሎት ጊዜ ሊያልፍባቸው ሶስት ወር ሲቀራቸው የደረሳቸው በመሆኑ፤ ኢንስቲትዩቱ ኬሚካሎቹ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሳያልፍ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ስለነበረበት የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

64. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች እንደተገዙ ለማዕከላቱ ማስተላለፍ ስለነበረበት እና ግብአቶች የመጠቀሚያ ጊዜ መቼ እንደሚያበቃ ለማወቅ ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ አለመተግበሩ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

65. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ለተገዙበት አላማ መዋላቸውን ባለመከታተሉ በውጭ ምንዛሪ የተገዙ ከሚካሎች የመጠቀሚያቸው እንዲያበቃ እና የአገር ሀብት ጠቅም ላይ እንዳይውል አድርጓል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና የኬሚካል ምርቶችን የሚያስወግድ መሆኑን በተመለከተ፤**

66. ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈ ምርቶችን ሊያስወግድ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

❖ ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና የኬሚካል ምርቶችን ያላስወገደ መሆኑን፤ ለአብነት፡-

☞ በኢንስቲትዩቱ ሰበታ መጋዝን ዴልታሜትሪን 1% 40 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20% 160 ሊትር፤ በጠቅላላ 200 ሊትር ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ፣ በአርባ ምንጭ እንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል ዴልታሜትሪን 1% 604 ሊትር እና ዴልታሜትሪን 20% 2646 ሊትር በጠቅላላ 3250 ሊትር ፤ እንዲሁም በአሶሳ እንስሳት ጤና ማዕከል ዴልታሜትሪን 20%= 268 ሊትር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎችን ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ፣ እንዲሁም ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ያቆሙ ሁለት ኒሳን ፓትሮል መኪናዎች የሰሌዳ ቁትር ኮድ 4-01030 እና 4-03455 ሁለት ሱዙኪ ሞተሮች፤ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-4333፤ ኮድ 4-4342፤ አንድ ያማሃ ሞተር የሰሌዳ ቁጥር 4-4341፤ ያልተወገዱ መሆኑ፤

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፤ከመስክ ምልከታ እና ከቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች በኢንስቲትዩቱ አቅም የሚወገዱ ስላልሆኑ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንደሚያስወግዱት እና ሌሎች ንብረቶች በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር በኩል የሚፈፀም መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

69. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ኢንስቲትዩቱ በአርባ ምንጭ ማዕከል እና በሶዶ ማስተባበርያ ጣቢያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎችንም ሆነ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የቆሙትን ተሽከርካሪዎችን ለማስወገድ ያደረገውን ጥረት የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልንም፡፡

70. ኢንስቲትዩቱ በማዕከሎች የሚገኙ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና የኬሚካል ምርቶችን ለማስወገድ ጥረት አለማድረጉ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

71. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና የኬሚካል ምርቶች በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዳይወገድ አድርጓል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራቱን በተመለከተ፣

72. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከክልሎች፣ከዞኖች እና ከወረዳዎች ጋር በጋራ ሊያቅድና ሊገመግም ይገባል፡፡

73. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡- በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ ከመስክ ምልከታ እና ከቃለ-መጠይቅ፣

- ☞ ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ከክልሎች ጋር የምክክር መድረክ በ2014 እና 2015 በጀት ዓመት ያዘጋጀ ቢሆንም በ2016 በጀት ዓመት ያላዘጋጀ መሆኑ፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከዞኖች እና ከወረዳዎች ጋር በጋራ እቅድ የማያቅድና የማይገመግም መሆኑ፣
- ☞ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት የጋሞ ዞን፣ የወላይታ ዞን፣ የምህራብ አባያ ወረዳ፣ የአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ የጎፋ ወረዳ እና የአበላ አባያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ አቅረቦ በሰጡተ መልስ፡- አርባ ምንጭ ማዕከልም ሆነ ሶዶ ማስተባበሪያ ጣቢያ፣የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራን በተመለከተ ከዞኖች እና ከወረዳዎች ጋር በጋራ እቅድ ስለማያቅዱ ስለሚያከናውናቸው ዝርዝር ሥራዎች እንደማያውቁ የዞን እና የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

74. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ በቆላ ዝንብ ቁጥጥር ሥራዎች ላይ በትብብር መስራት በተለይም በወረዳ በኩል የሙያ ድጋፍ፣

በዞኖች በኩል የመኪና ትብብር የሚደረግ ሲሆን በቀጣይ በጋራ የሥራ ውይይት ለማድረግ ዕቅድ መያዙን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

75. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራን በዋነኛነት የሚከናወነው በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በመሆኑ በተመለከተ የሚያቅዳቸውንና የሚያከናውናቸውን ሥራዎች ከዞኖች እና ከወረዳዎች ጋር በጋራ እቅድ በማቀድ ወይም ግብዓት በማሰባሰብ በዞኑ፣በወረዳው እና በቀበሌዎቹ ስለሚያከናውናቸው ዝርዝር ሥራዎች የማያሳውቃቸው በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

76. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከዞኖች እና ወረዳዎችን እንደ ዋና ባለድርሻ አካል አለመውሰዱ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

77. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን በዋነኝነት በቆላ ዝንብ ተጠቂ የሆኑት እንስሳት የሚገኙትና የመከላከል የሚሠራባቸው ከዞኖች እና ከወረዳዎች ብሎም በቀበሌ ደረጃ በመሆኑ አብሮ ለማቀድና ግብዓት አለማሰባሰብና በጋራ አፈፃፀሙን የማይገመግም በመሆኑ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቅንጅታዊ የቁጥጥር ሥራ የላላ እንዲሆንና የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ አድርጓል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ ለአርሶአደር፣ ለአርብቶአደርና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠቱን በተመለከተ፣**

78. ኢንስቲትዩቱ ለአርሶአደር፣ አርብቶአደርና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡

79. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ☞ ኢንስቲትዩቱ ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድርስ በእቅድ ላይ የተመሰረተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ያልሰጠ መሆኑ፣

- ☞ የኦዲት ቡድኑ በመስክ በመገኘት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን የወላይታ ዞን ውስጥ ያሉ የአበላ አባያ ወረዳ፣ አባያ ጮውካሬ ቀበሌ

ከብቶቻቸውን ኬሚካል ለማስቀባት /ለማስረጨት/ የመጡትን አርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮችን ተጠይቀው በሰጡተ መልስ፣-በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ከብቶቻችንን ኬሚካል ለማስቀባት/ ለማስረጨት/ ከመገናኘት ውጭ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስለሚያደርሰው ጉዳት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንዳልተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

☞ እንዲሁም በጋሞ ዞን፣ ለምዕራብ አባያ ወረዳ፣ ለአርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ፣ በወላይታ ዞን፣ ለኦፋ ወረዳ እና ለአበላ አባያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣- በኢንስቲትዩቱ /በማዕከሉ/ በማስተባበሪያ ጣቢያው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በተደራጀና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ የማይሰጥ መሆኑን፣ ነገር ግን የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በርጭትና በክትባት ወቅት በቂ ባይሆንም እንደሚሰጥ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኦዲት ቡድኑ በአበላ አባያ ወረዳ፣አባያ ጮውካሬ ቀበሌ በሦስት ርጭት ቦታ ተገኝቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሲሰጥ አልተመለከተውም፡፡

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች፣ከመስክ ምልከታ እና ከቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ቅንጅታዊ ሥራዎች መካከል የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ወይም ሥልጠና በየዓመቱ ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ እና በሪፖርት ውስጥም በግልጽ የተቀመጠ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

81. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡

☞ ኢንስቲትዩቱ /ማዕከሉ/ /ማስተባበሪያ/ ጣቢያው ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድርስ በእቅድ ላይ የተመሰረተ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ስሰጥ የኦዲት ቡድኑ በአበላ አባያ ወረዳ፣አባያ ጮውካሬ ቀበሌ በሦስት ርጭት ቦታ ተገኝቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሲሰጥ ያልተመለከተ እና

ህብረተሰቡንም ጠይቆ ከ2014 ዓ.ም ጅምሮ በተከታተይ እንደማይሰጣቸው ጠይቆ በመረዳቱ በየዓመቱ በዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው የሚለውን ምላሽ የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

82. ኢንስቲትዩቱ ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመታት በተከታታይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አለመስጠቱ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

83. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ከ2014 እስከ 2017 ሩብ በጀት ዓመት ድርስ በእቅድ ላይ የተመሰረተ እና ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ያልሰጠ በመሆኑ አርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራውን እንዳያግዙ አድርጓል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን የሰራ ስለመሆኑ፣**

84. ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ እንዲካሄድ ማህበረሰቡን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላትን ለማሳተፍ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ እንዲካሄድ ማህበረሰቡን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላትን በማሳተፍ በተለይም በቆላ ዝንብና በገንዲ በሽታ በሚጠቁ አካባቢዎች በሚገኙ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ተከታታይነት ባለው መልኩ ያልሰራ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ በሰው ላይ የተከሰተው የእንቅልፍ በሽታ /HAT/Human African Tryponosomiasis /Sleeping Sickness/ በጆርናል ላይ ጥናት ባደረጉ አካላት በኩል የታተመ መሆኑ፣ ከሊጋሽ

ድርጅት በመጡ ባለሙያዎች በኩልም ከህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና አርባ ምንጭ ማዕከል ለተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ መሆኑ፤ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ችግር በክልሎች ሚዲያ በተለያዩ ጊዜያት ሲቀርብ የነበረ መሆኑ፤ በኢንስቲትቱ በኩልም የችግሩ ስፋት እና እየተደረገ ያለው ጥረት በተደጋጋሚ ሚዲያ ላይ የቀረበ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

87. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ለራሳቸው ባለሙያዎች ስለተሰጠ ግንዛቤ እንጂ ለህብረተሰቡ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም ግንዛቤ ስለመስጠታቸው ምላሽ ባለመስጠታቸው የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

88. ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ እንዲካሄድ ማህበረሰቡን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላትን በማሳተፍ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ተከታታይነት ባለው መልኩ አለመስራቱ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

89. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ የገንዲ በሽታ በሰዎች ላይ በሚያደርሰው ጉዳት ዙሪያ ትኩረት በመስጠት ለበሽታው ተጋላጭ ለሆኑ ማህበረሰቦች የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምርት አለመስጠቱ ዘላቂ የቁጥጥር ሥራዎችን ህብረተሰቡ አጋዥ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያግዝ መረጃ የሚያመነጭ እና የሚያደራጅ ስለመሆኑ፤


90. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያግዝ መረጃ ሊያመነጭና ሊያደራጅ ይገባል፡፡

91. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-


- ❖ ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ የተተከሉ ወጥመዶች ብዛት ዝቅተኛ መሆኑ፤ እንዲሁም ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማዕከላት የሚያመነጩት መረጃ፤ ተደራሽ፤ ጥራቱን የጠበቀ እና ማዕከላት የተሰጣቸውን ሁሉንም የስራ አካባቢ /Operational area/ የማይሸፍን መሆኑ፤ ለአብነት፡-

    - ☛ በ2014 ዓ.ም 620 መረጃዎችን ለማሰባሰብ አቅዶ 254 መሰረታዊ መረጃ በማሰባሰብ 41 በመቶ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፤ በ2015 ዓ.ም 991 መረጃዎችን

ለማሰባሰብ አቅዶ 722 መሰረታዊ መረጃ በማሰባሰብ የዕቅዱን 72.8 በመቶ ያከናወነ መሆኑ፤ በ2016 ዓ.ም 1070 ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ አቅዶ 197 መሰረታዊ መረጃ በማሰባሰብ የዕቅዱን 18.4 በመቶ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፤




- ኢንስቲትዩቱ ከ2014 እስከ 2016 በጀት ዓመት የታቀዱ እቅዶች የኢንስቲትዩቱን መሪ እቅድ መነሻ ያላደረጉ መሆኑ፤ለማሳያ፡ በስትራቴጂክ ዕቅድ (2013-2022) በየዓመቱ 1340 ወጥመዶችን ለመትከል ከተቀመጠውና ከ2014 እስከ 2016 በጀት ዓመት አከናውናለሁ ብሎ ካስቀመጠው እቅድ ጋር ሲነፃፀር በቅደም ተከተል በ2014 ዓ.ም እቅድ 1340 አፈፃፀም 254፤18.9 በመቶ፤ በ2015 ዓ.ም እቅድ 1340 አፈፃፀም 722፤ 53.8 ከመቶ እና በ2016 ዓ.ም እቅድ 1340 አፈፃፀም 197፤ 14.7 ከመቶ ብቻ የፈፀመ መሆኑ፤




በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ከቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

92. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ተደራሽነቱ በፀጥታ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር አቅም በፈቀደ መሠረት ማዕከላት በቆላ ዝንብ ተጠቂ የሆኑት አካባቢዎች ለመሸፈን ጥረት እያደረጉ እንደሆነ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

93. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ፡ ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ የተተከሉ ወጥመዶች ብዛት ዝቅተኛ በመሆኑ፤ ለቅድመ ቆላ ዝንብ የሚሰበሰበው መሰረታዊ መረጃ ወካይ የማይሆን በመሆኑ፤ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማዕከላት የሚያመነጩት መረጃ፤ ተደራሽ፤ ጥራቱን የጠበቀ አለመሆኑ፤የቆላ ዝንብ ምንጭ የሆኑ ፓርኮች መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የማይካተት በመሆኑ፤ ማዕከላት የተሰጣቸውን ሁሉንም የስራ አካባቢ /Operational area/ የማይሸፍኑ መሆኑ፤የአርባ ምንጭ ማዕክል እንዲሸፍን ከተሰጠው ተጠቂ ከሆኑ 90 ወረዳዎች ውስጥ 45 በመሸፈን 50 ከመቶ ብቻ የፈፀመ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

94. ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ የተተከሉ ወጥመዶች ብዛት ዝቅተኛ መሆኑ፤ እና መረጃዎቹ ከሁሉም አካባቢ ወካይ አለመሆናቸው እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

95. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ የተተከሉ ወጥመዶች ብዛት ዝቅተኛ በመሆኑ፤ እና ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማዕከላት የሚያመነጩት መረጃ፤ ተደራሽ፤ ጥራቱን የጠበቀ እና ማዕከላት መረጃዎቹ ከሁሉም አካባቢ ወካይ ባለመሆናቸው የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ሥራ መሰረታዊ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

**በኢንስቲትዩቱ፤ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የሚታወቅና የአሠራር ስርዓት የተዘረጋለት ስለመሆኑ፤**

96. በኢንስቲትዩቱ፤ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ እንዲታወቅ የአሠራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

97. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የማይታወቅ፣ የአሠራር ስርዓት ያልተዘረጋለት መሆኑን፣ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ሰነዶች እና ጉዳዩ ፣ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

98. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፣ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ፡- የኢንስቲዩቱና የክልሎች ተግባርና ኃላፊነት ተለይቶ በሰነድ እንዲዘጋጅ የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን እና የተጀመሩት ሰነድ የማዘጋጀትና የጋራ የማድረግ በቀጣይ የሚሰራ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

99. በኢንስቲትዩቱ እና በክልሎች ጋር በመተባበር የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ድርሻ ምን እንደሆነ አለመለየቱ እና የአሠራር ስርዓት አለመዘርጋቱ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

100. በመሆኑም በኢንስቲትዩቱ፣ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የማይታወቅ፣ የአሠራር ስርዓት ያልተዘረጋለት መሆኑ የሚሠራው ስራ ተጠያቂነትን እንዳያስከትል አድርጓል፡፡

**ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፣ በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስተባብርና ስራዎቻቸውንም የሚያቀናጅ ስለመሆኑ፣**

101. ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፣በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ሊያስተባብርና ስራዎቻቸውንም ሊያቀናጅ ይገባል፡፡

102. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ☞ ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፣ በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ያላስተባበርና ስራዎቻቸውንም ያላቀናጀ መሆኑ፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ በፓርኮች ውስጥና አካባቢው የሚገኙ የዱር እስሳትን ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት የማይሰራ መሆኑ፣

☞ በኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠር ከማእከል የሚደረገው የማስተባበር፤ የድጋፍ እና ክትትል ሥራ ጠንካራና የተሟላ አለመሆኑን ከተከለሱ ሰነዶች እና ጉዳዩ ፣ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. ስለጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ፤ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ፤ በረቂቅ ሪፖርት እና በውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት መልስ ማዕከላት ከክልሎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች ጋር በቅርበት አብሮ ስለሚሰሩ ተባብሮ የመሥራት ጠንካራ ግንኙነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ኢንስቲትዩቱ የማስተባበርና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲያስፈልግ ከክልሎች እና ከዞኖች ጋር አብሮ እየሰራ እና ማዕከላትን እየደገፈ እንደሚገኝ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

104. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን ለመቆጣጠር ከማእከል የሚደረገው የማስተባበር፤ የድጋፍ እና ክትትል ሥራ ጠንካራና የተሟላ ባለመሆኑ እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት የማይሰራ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

105. ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፤በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር አለማስተባበሩና ስራዎቻቸውንም አለማቀናጀቱ እንደምክንያት ተወስደዋል፡፡

106. በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፤በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር የማያስተባበርና ስራዎቻቸውንም የማያቀናጅ በመሆኑ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

107. ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የተቻለ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የአሠራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች በመኖሩ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ /Road map/ አልተዘጋጀም፤ ኢንስቲትዩቱ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠርና ማጥፋት ሥራ የተዘጋጀው የኢንስቲትዩቱ በየአመቱ ለመስራት በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ላይ የተቀመጡት መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የሚጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ስፋት፣ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከል፣ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት ስፋት፣ መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች ብዛት፣ በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆች ተከላን፣ የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በእንስሳት ጀርባ መቀባትን፣ መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ርጭትን በተመለከተ፤ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር የተከናወነባቸው ወረዳዎች ብዛት፣ ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል ትራፖችን/ ወጥመዶችን በመትከል በተያዙት ላይ ጥናት ማካሄድን የሚመለከቱ  ዕቅዶች ወደ አመታዊ ዕቅድ ሲመነዘሩ በማሳነስ የታቀዱ እና አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ መሆኑ፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን ቆላማና ከፊል ቆላማ የስራ አካባቢን /Operational area/ መሠረት በማድረግ የስርጭት ካርታ አዘጋጅቶ ለዋናኛ ባለድርሻ አካላት ተደራሽ አላደረገም፣ በየጊዜውም ካርታውን ወቅታዊ አላደረገም፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንቦችን መቆጣጠሪያና ማጥፊያ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አቀናጅቶ የመጠቀም ሥራው አነስተኛ ነው፣
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን አላከናወነም፣

- ኢንስቲትዩቱ ከገንዲ በሽታ ስርጭት ጋር በተያያዘ የአስተላላፊ ዝንቦችንና ሌሎች ለበሽታው መሰራጨት በምክንያትነት የሚነሱ ስነ-ምህዳራዊ ምክንያቶች ጥናት መሠረት ተመራጭ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች ተግባራዊ አላደረገም፡፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፤ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውል ግብዓቶች በተለይ የዴልታሜትሪን 1% ኬሚካል አቅርቦት ኬሚካሉን መቀባት ከሚያስፈልጋቸው የእንስሳት ብዛትን (Animal Population) አንጻር በጣም አነስተኛ ነው፣ ዴልታሜትሪን 20% ኬሚካል አቅርቦት ባለመኖሩ እና በወረዳዎች የታርጌት ተከላ አልተከናወነም፣
- ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ ግብዓቶች ሥራ ላይ ሳይውሉ የመጠቀሚያቸው ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች መኖራቸው እና እንዲወገዱ አልተደረገም እንዲሁም ሌሎች መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ሳይወገዱ ተገኝተዋል፤
- ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከዞኖች እና ከወረዳዎች ጋር በጋራ እቅድ የማያቅድና ወይም ያቀዳቸውን ስራዎች ዝርዝር የማያሳወቃቸው እና አፈፃፀሙንም በጋራ አይገመግምም በመሆኑ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ በቅንጅት እንዳይሰራና የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ስራ የተፈለገውን ውጤት አለማምጣቱ፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለአርሶ፤ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ዙሪያ ዕቅድ በመያዝ በየግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አልሰጠም፣
- ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር መሰረታዊ መረጃ ለማሰባሰብ የተተከሉ ወጥመዶች ብዛት ዝቅተኛና ወካይ አለመሆናቸው፣ በማዕከላት የሚሰበሰበው መረጃም የተሰጣቸውን ሁሉንም የስራ አካባቢ /Operational area/ አይሸፍንም፤
- በኢንስቲትዩቱ፤ በክልል፣ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ የማይታወቅና የአሠራር ስርዓት አልተዘረጋለትም፣
- ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፤ በዱር እንሳት ፓርኮች፣ ከአካባቢ አስተዳደር አካላት መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር የማስተባበርና ስራዎቻቸውንም የማቀናጀት ሥራው ደካማ መሆኑ፣

የሚሉ ናቸው፡

በመሆኑም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል 4 አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

108. የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም በውጤታማነት እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ☞ ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን የመከላከልን የቁጥጥር ሥራውን የሚያግዝ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ፍኖተ ካርታ ሊያዘጋጅና እርሱን ወደ ስትራቴጂክ ዕቅድ በመቀየር ሊተግብር ይገባል፡፡
- ☞ የኢንስቲትዩቱ በአስር አመቱ መሪ ዕቅድ ላይ ለማከናወን ያቀዳቸውን ነገር ግን ከመሪ ዕቅዱ አንጻር ዕቅድ አፈጻጸማቸው አነስተኛ የሆኑት፣ መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የሚጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ስፋት፣ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከል፣ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት ስፋት፣ መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ዝርያዎች ብዛት፣ በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተነከሩ ታርጌት ጨርቆች ተከላን፣ የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በእንስሳት ጀርባ መቀባትን፣ መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ርጭትን በተመለከተ፤ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የቁጥጥር ተግባር የተከናወነባቸው ወረዳዎች ብዛት፣ ለቆላ ዝንብ አሰሳና ክትትል ትራፖችን/ ወጥመዶችን በመትከል በተያዙት ላይ ጥናት ማካሄድን በቀሪው የመሪ ዕቅዱ አመታት እንዴት ማካካስና ዕቅዱን ለማሳካት የሚቻልበተን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ስልት በመቀየስና ወደ ትግበራ ሊገባ ይገባል፡፡
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን የሚያሳይ ካርታ የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂ ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያዘጋጅ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊያሳውቅ እና በየጊዜውም ካርታውን ወቅታዊ ማድረግ የጠበቅበታል፡፡
- ☞ ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ቴክኖሎጂዎችን (የመከኑ ዝንቦችን መልቀቅ ጨምሮ)፤ ኬሚካል የተቀቡ የታርጌት ጨርቆችን መትከል፤ ትራፖችን መትከል፤ መሬት ለመሬት የኬሚካል ርጭት ማካሄድ፤ በአይሮፕላን የኬሚካል ርጭት ቴክኖሎጂዎችን እንደየነባራዊው ሁኔታ መሰረት

በማድረግ አቀናጅቶ ሊጠቀምና የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡


- ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን በማጥናት እና የጠገኙ መልካም ነገሮችን ሊቀምርና ሊያሳድግ የተከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ካሉም የሚቀረፉበትን ስልት ሊቀይስ ይገባል፡፡ ኢንስቲትዩቱ ከገንዲ በሽታ ስርጭት ጋር በተያያዘ የአስተላላፊ ዝንቦችንና ሌሎች ለበሽታው መሰራጨት በምክንያትነት የሚነሱ ስነ-ምህዳራዊ ምክንያቶችን በማጥናት ተመራጭና አዋጭ የሆኑ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ሊቀይስ እና ተፈፃሚነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፣ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ እና በዕቅድ ያያዛቸውን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችና ኬሚካሎች ፍላጎት ጥናት ስትራቴጂካዊ የግዥ ዕቅድ በማዘጋጀት ግዥ ሊያከናውን እና የተገዙትም በተገቢው መንገድ ሊሠራጩና ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ብክነትን ጭምር መከላከል ይጠበቅበታል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የአገልግሎት መስጫ ጊዜያቸው ኬሚካሎችን ከሚመለከታቸው እና የማስወገድ ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት ጋር በመመካከር ሊያስወግድ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በኢንስቲትዩቱ ያሉ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና በተቀመጠው የህግ አግባብ መሰረት ሊያስወግድ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታና ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከክልሎች፣ከዞኖች እና ከወረዳዎች ለዕቅድ የሚሆን ግብዓት ሊሰበሰብ፣ ጋር በጋራ ሊያቅድና አፈጻጸሙን ሊገመግም ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ከሚመለከታቸው የክልል። የዞንና የወረዳ አካካላት ጋር በመተባበር ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለመላው ህብረተሰብም የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያግዝ መረጃ የሚሰበሰብበትን ሥርዓት በመዘርጋትና መረጃ ሊያመነጭና ሊያደራጅ ይገባል፡፣ውጤቱንም ለሚመለከታቸው ፖሊሲ አውጪዎች፣ ተመራማሪዎችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

☞ በኢንስቲትዩቱ፤ በዞኖች እና ወረዳዎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ  ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ ሊታወቅና የአሠራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡


☞ ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት፤በዞኖች እና በወረዳዎች መካከል ያለው  የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር  ስራ ባለድርሻ ከሆኑት የክልል፣ የዞን፣ እና የወረዳ፣ ከዱር እንስሳት ፓርኮች እና ከምርምር ተቋማት ጠንካራ ግንኙነት የቆላ ዝንብ እና የገንዲ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ሥራውን ሊያስተባብርና ስራዎቹ ውንም ሊያቀናጅ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት እና የማዕከላት የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፤ እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡

## አባሪ 1፡ የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ድርጅታዊ መዋቀር



# አባሪ 2፡ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር መዋቅር



## አባሪ ሦስት 3 የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡ <u>በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት</u>**

**የኦዲቱ አካባቢ፡ <u>የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ሥራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ፤</u>**

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| I. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት እንዲሁም የምርምር ሥራ አፈፃፀም ውጤታመነትን መገምገም፤ | 1. ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ሊያጠናና ሊተነትን ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 2. ኢንስቲትዩቱ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቆላ ዝንብ ዝርያዎችንና የገንዲ በሽታ ህዋስ ስርጭትን ለመከላከልና ለማጥፋት የስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 3. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሽፋን ሊያሳድግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ እቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች** (2014-2016) |
| | 4. ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መከላከል ስራዎች የተገኙትን ውጤቶች ሊገመግም ይገባል፡፡ (**ምንጭ፡-ከኢንስቲትዩቱ እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት** (2014 -2016) |
| | 5. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ስርጭትን የጂ፣አይ.ኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የስርጭት ካርታ ሊያዘጋጅና በየጊዜው ሊያሻሽል ይገባል፡፡ **ምንጭ ከኢንስቲትቱ የሥራ መዘርዝር** |
| | 6. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ስራ ላይ ውለው ውጤታማ ሆኖ የተገኙና በአከባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀም ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 7. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንቦችን በብዛትና በጥራት በሰው ሰራሽ አሰራር በማራባት እና ወንድ የቆላ ዝንቦችን በጨረር ኃይል በማምከን የተመረጡት አካባቢዎች በመልቀቅ የመጨረሻውን ዝንብ የማጥፋት ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 8. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ እያስከተለ ያለውን ጉዳት፣ የቁጥጥሩ ስራ ለህብረተሰቡ ባስገኘው ጥቅም ዙሪያ ሶሽዮ-ኢኮኖሚያዊ ጥናቶችን ቀርፆ ጥናትና ምርምር ሊያካሄድ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ ሥራ መዘርዝር** |
| | 9. ኢንስቲትዩቱ ከገንዲ በሽታ ስርጭት ጋር በተያያዘ የአስተላላፊ ዝንቦችንና ሌሎች ለበሽታው መሰራጨት በምክንያትነት የሚነሱ ስነ-ምህዳራዊ ምክንያቶችን በማጥናት ተመራጭ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ሊቀይስ እና ተፈፃሚነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ ሥራ መዘርዝር** |
| II. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ለመከላከል በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ግዥዎች፣ ሥርጭት እና የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ስርዓት ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም፣ | 10. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ፣ መከላከልና ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ፍላጎት ጥናት ሊሰበስብ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡ የመንግስት የግዥ መመሪያ** |
| | 11. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጥፍያ የተመደበለትን በጀት ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊጠቀም ይገባል፡፡<br>ምንጭ መልካም ተሞክሮ |
| | 12. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና መከላከልና የገንዲ በሽታ ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ፍላጎት የስትራቴጂክና አመታዊ የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡ የመንግስት የግዥ መመሪያ |
| | 13. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራዎች የሚውሉ የግብዓቶች ስፔስፊኬሽን ስታንዳርዱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ሊያደርግ እና ተግባራዊነቱንም ሊከታተል ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የኢንስቲቲ የሥራ መመሪያ** |
| | 14. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጥፍያ አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት ግዥዎችን በእቅዱ መሰረት ሊፈፅም ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የመንግስት ግዥ መመሪያ** |
| | 15. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ማጥፍያ አገልግሎት የተገዙ ግብዓቶችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የመንግስት ግዥ መመሪያ** |
| | 16. ኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ንብረቶችንና ተረፈ ምርቶችን ሊያስወግድ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- የንብረት አያያዝ መመሪያ** |
| III. ኢንስቲትዩቱ በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ በተጠቁ የአገሪቱ አካባቢዎች የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና የማጥፋት ስራዎች ዙሪያ ሕብረተሰቡ | 17. ኢንስቲትዩቱ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ከክልሎች ጋር በጋራ ሊያቅድና ሊገመግም ይገባል፡፡ (**ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 18. ኢንስቲትዩቱ ለአርሶ፣ አርብቶ እና ከፊል አርሶና አርብቶ አደሮች በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡ (**ምንጭ፡-ከኢንስቲትዩቱ ሥራ መዘርዝር እና ከመሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 19. ኢንስቲትዩቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር የሚያግዝ መረጃ ሊያመነጭና ሊያደራጅ ይገባል፡፡<br>(**ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |

| የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) | የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) |
|---|---|
| የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኝ ስለመደረጉና የባለድርሻ አካላት ተሣታፊ ስለመሆናቸው መገምገም፡፡ | 20. ኢንስቲትዩቱ ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬትን ከዳግም ወረራ በመከላከል መሠረታዊ መረጃ በማሰብሰብ አዳዲስ የቁጥጥር ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመትመሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 21. ኢንስቲትዩቱ ውጤታማ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምርና ቁጥጥር ስራ እንዲካሄድ ማህበረሰቡን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላትን ለማሳተፍ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲሰሩ ሊያስተባብር ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-ከኢንስቲትዩቱ ሥራ መዘርዝር እና ከመሪ ዕቅድ** (2013-2022) |
| | 22. በኢንስቲትዩቱና በክልሎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ ሊታወቅና የአሠራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የአሥር ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ** (2013-2022) |
| | 23. ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላትና በክልሎች መካከል ያለው የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥርና ምርምር ስራ ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖር ሊያስተባብርና ስራዎቻቸውንም ሊያቀናጅ ይገባል፡፡ (**ምንጭ፡-ከኢንስቲትዩቱ የአሥር ዓመት መሪ ዕቅድ** (2013-2022) |

## አባሪ 4 ፡ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር የሥራ ፍሰት

**1. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር ም/ዋና ዳይሬክተር**

የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር ም/ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

በስሩ የሚገኙ ማዕከላትን በማስተባበር ስልታዊና አመታዊ እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

**2. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማስተባበሪያ ዴስክ**

የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማስተባበሪያ ዴስክ ተጠሪነቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር ም/ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት በስሩ የሚገኙ ባለሙያዎችን በማስተባበር እና ከማዕከላት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት የመፍጠር ተግባራት ይሰራል፡፡

**3. የቃሊቲ ቆላ ዝንብ ምርምር ማዕከል ተግባር**

ቃሊቲ የቆላ ዝንብ ምርምር ማዕከል የቆላ ዝንብ ዝሪያዎችን በላቦራቶሪ ውስጥ በማርባትና በኃላም ወንድ የቆላ ዝንቦች በመለየት በጨረር ኃይል በማምከን በሀገራችን የመካን ነፍሳት ቴክኖሎጂ ስራዎች ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር ማዋል ፡፡

የቃሊቲ ቆላ ዝንብ ምርምር ማዕከል ተጠሪነቱ ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር ም/ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- ማዕከሉን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ በስሩ ያሉት ዴስኮችን በማስተባበር ሥራዎችን ያቅዳል፣ ያስተባብራል፣ ውሳኔ በሚያሥፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
- በማዕከሉ የሚከናወኑትን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ተግባራትን በደንብና መመሪያዎች መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

**4. የአራቱ የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት ተግባር**

የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከላት ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ምርምር ም/ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ አሰሳና ቅኝት መረጃን በማደራጀት፣ የተቀናጀ የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ከስሩ የተዋቀሩት ዴስኮችና ጣቢያዎችን በማስተባበር እንዲሁም ከሌሎች የክልል፣ የዞንና የወረዳዎች የእንስሳት ዘርፍ ተቋማት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነትን በመፍጠር የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት የሚሰሩ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 1፡- **መሠረታዊ መረጃ ተሰብስቦ የቁጥጥር ሥራ የተጀመረባቸው አዳዲስ መሬቶች ሥራ አፈፃፀም የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | አመታዊ ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ክንውን | ከአመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | የአሥር ዓመት ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ከአሥር ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 | 10,976 | 11,058 | +100 | 17,746 | 62.3 (11,058) |
| 2015 | 11,000 | 4,700 | 42.7 | 15,777 | 29.7 (4,700) |
| 2016 | 9,346 | 3,650 | 39.1 | 15,871 | 22.9 (3,650) |
| ድምር | 31,322 | 19,408 | 61.96 | 49,394 | 39.29 (19,408) |

ሰንጠረዥ ሁለት፡- **የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ መከላከል ሥራ አፈፃፀምን የሚያሳይ፡፡**

| ተ.ቁ | በቆላ ዝንብ አማካይነት በሚተላለፈው የገንዲ በሽታ የተጠቁ አካባቢዎች | የሚሸፍኑት ስፋት በካሬ .ኪ.ሜ፣ |
|---|---|---|
| 1 | በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል (አሁን ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች) | 68,000 |
| 2 | በኦሮሚያ ክልል | 66,000 |
| 3 | በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል | 35,000 |
| 4 | በጋምቤላ ክልል | 20,000 |
| 5 | በአማራ ክልል | 11,000 |
| | ድምር | 200,000 |

ሰንጠረዥ ሦስት፡- **ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት አፈፃፀምን የሚያሳይ፡፡**

| | አመታዊ ዕቅድ ክንውን | | | በአሥር ዓመት ዕቅድ በአመቱ ለማከናወን የታቀደውና ክንውን በካ.ኪ.ሜ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዓ.ም | አመታዊ ዕቅድ በቁጥር | ክንውን | ከአመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | በአሥር ዓመት ዕቅድ ለአመቱ የታቀደው በካ.ኪ.ሜ | ከአሥር ዓመት ዕቅድ አንጻር የአመቱ አፈጻጸም | አፈጻጸም በመቶኛ |
| 2014 | 72,202 | 50,338.95 | 70 | 87,800 | 50,338.95 | 57.3 |
| 2015 | 80,000 | 51,277 | 64.1 | 110,520 | 51,277 | 46.39 |
| 2016 | 35,000 | 35,517 | +100 | 114,605 | 35,517 | 30.9 |
| ድምር | 187,202 | 137,132.95 | 73.25 | 312,925 | 137,132.95 | 43.82 |

ሰንጠረዥ አራት፡- **መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ (የግሎሲና ፉስኪፐስ) ብዛት የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | አመታዊ ዕቅድ በቁጥር | ክንውን በቁጥር | ከአመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | የአሥር ዓመት ዕቅድ በቁጥር | ከአሥር ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 | 202,000 | 86,300 | 43 | 1,595,400 | 5.4 (86,300) |
| 2015 | 186,472 | 147,123 | 78.9 | 1,595,724 | 9.2 (147,123) |
| 2016 | 211,932 | 288,070 | +100 | 1,559,745 | 18.4 (288,070) |
| ድምር | 600,404 | 521,493 | 86.85 | 4,750,869 | 10.97 (521,493) |

ሰንጠረዥ አምሥት:- **መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ (የግሎሲና ፓሊዲፐስ) ብዛት የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | አመታዊ ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ክንውን | ከአመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ | የአሥር ዓመት ዕቅድ በቁጥር | ከአሥር ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2014 | 250,000 | 328,490 | +100 | 1,700,760 | 19.3 (328,490) |
| 2015 | 370,000 | 533,193 | +100 | 1,702,106 | 31.3 (533,193) |
| 2016 | 632,045 | 305,759 | 48.37 | 1,702,126 | 5.2 (305,759) |
| ድምር | 1,252,045 | 1,167,442 | 93.24 | 5,104,992 | 22.86 (1,167,442) |

ሰንጠረዥ ስድስት:- **በፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል ተነክሮ የተተከሉ ታርጌት ጨርቆች ቁጥርን የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | ዕቅድ በቁጥር | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 36,723 | 3,281 | 8.9 |
| 2015 | 32,000 | 369 | 1.2 |
| 2016 | 4,000 | 0 | 0 |
| ድምር | 72,723 | 3,650 | 5.01 |

ሰንጠረዥ ሰባት:-**የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተቀቡ እንስሳትን የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | ዕቅድ በቁጥር | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 3,133,600 | 1,389,598 | 44.4 |
| 2015 | 3,620,000 | 1,590,605 | 43.9 |
| 2016 | 3,880,000 | 1,661,528 | 43 |
| ድምር | 10,633,600 | 4,641,731 | 43.65 |

ሰንጠረዥ ስምንት:-**መሬት ለመሬት የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል የተረጨ (በካ.ኪ.ሜ) የሚያሳይ፡፡**

| ዓ.ም | ዕቅድ በካ.ኪ.ሜ | ክንውን | አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2014 | 18,900 | 180 | 1.0 |
| 2015 | 23,800 | 0 | 0 |
| 2016 | 1500 | 0 | 0 |
| ድምር | 44,200 | 180 | 0.40 |